# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

## ጋዜጣዊ መግለጫ

ሚያዝያ 18 / 2008 ዓ.ም.

### መንግሥት ለዜጎች ሕይወት፣ አካል፣ ንብረትና ነጻነት በቂ ጥበቃ ያድርግ!

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት ክፍል አንድ አንቀጽ 14 ‹‹ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሠሥ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነትና የነጻነት መብት አለው›› በማለት በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀችው የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ ሦስት ‹‹እያንዳንዱ ሰው የሕይወት፣ የነጻነትና የተሟላ ደኅንነት መብት አለው›› በማለት በማያሻማ መልኩ ደንግጓል፡፡

ይህንን የዜጎችን የሕይወት፣ የአካል ደኅንነትና ነጻነት መብቶች የመጠበቅ ኃላፊነት በግንባር ቀደምትነት የተጣለበት መንግሥት ነው፡፡ ይሁንና ይህንን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ መንግሥት በአግባቡ ባለማሟላቱ፣ ባለመጠበቁና ባለማክበሩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በንጹሐን ዜጎች ላይ ተፈጽመዋል፡፡

ዓርብ ሚያዝያ ሰባት ቀን 2008 ዓ.ም. በግምት ከንጋቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ በኢትዮጵያ ጋምቤላ ክልል ኑዌር ዞን ሦስት ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ 13 ቀበሌዎች ውስጥ ‹‹ከደቡብ ሱዳን የመጡ›› በተባሉ የታጠቁ የሙሩሌ ጎሣ አባላት በተፈጸመ ወታደራዊ ጥቃት ከ200 በላይ ንጹሐን ዜጎች በጥይት ተገድለዋል፣ ከ100 በላይ ዜጎች በጥይት ቆስለዋል፣ በርካታ ህጻናትና ሴቶች ተጠልፈው ተወስደዋል፤ ስቃይ እየተፈጸመባቸው መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል፡፡ በርካታ መኖሪያ ቤቶች ተቃጥለዋል፣ ከ2000 በላይ ከብቶች ተዘርፈዋል፣ በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎች በዚህ ጥቃት ምክንያት ለሕይወታቸው በመሥጋት ከቀያቸው ተፈናቅለው በተለያዩ አካባቢዎች ተጠልለዋል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) ይህንን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ፣ ደፋርና ሕገወጥ ድርጊት በጥብቅ ያወግዛል፡፡ በዚህ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ምክንያት ሕይወታቸውን ላጡ ዜጎች የተሰማውን ልባዊ ኃዘን እየገለጸ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው መጽናናትን ይመኛል፡፡

በጋምቤላ የተፈጸመውን ይህን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት አሳዛኝና በእጅጉ አሳሳቢ የሚያደርገው ጎረቤት ሐገር የሆነችው ደቡብ ሱዳን ያልተረጋጋችና የጸጥታ ችግር ያለባት መሆኑ እየታወቀ፣ ባለፉት ቅርብ ጊዜዎች ከደቡብ ሱዳን በሚመጡ ታጣቂዎች ተደጋጋሚ ግድያና ዝርፊያ እየተፈጸመ መሆኑ እየታወቀ፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ራሳቸውንና ንብረታቸውን የሚጠብቁበትንና የሚከላከሉበትን መሣሪያ በመንግሥት እንዲፈቱ መደረጋቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ ፖሊስና ልዩ ኃይል አባላት ትጥቅ እንዲፈቱ መደረጉ ድርጊቱን መከላከል እንዳይቻል አድርጎታል፡፡ ይህ ሕገ-ወጥ ድርጊት ከመፈጸሙ አስቀድሞ የአካባቢው ነዋሪዎችና ባለሥልጣናት የ‹‹ድረሱልንና ጥበቃ ይደረግልን›› ጥሪ እያቀረቡ እንደነበረና ነገር



የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ Human Rights Council

ግን መንግሥት ለዚህ ሥጋትና ተማጽኖ ተገቢውንና ፈጣን ምላሽ ባለመስጠቱ አሁን ለደረሰው ከፍተኛና ሰፊ እልቂት መፈጸም ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

መንግሥት፣ በተለያዩ የሐገሪቱ አካባቢዎች በተለያዩ ጊዜያት በታጣቂ ኃይሎች በንጹሐን ዜጎች ላይ የተፈጸሙትን አሰቃቂ ግድያዎችን አስመልክቶ የተለያዩ ምክንያቶችን ከመስጠት ይልቅ ከክስተቶቹ ትምህርት በመውሰድ በቀጣይ ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጸም በቂ ዝግጅት ሲያደርግ፣ አፋጣኝ፣ ዘላቂና አስተማማኝ የመፍትሔ እርምጃ ሲወስድ አይስተዋልም። ለዚህም ማሳያነት ይረዳ ዘንድ ከዚህ ቀደም የተፈጸሙትን ተመሳሳይ ሕገወጥ ድርጊቶች ማስታወስ ይቻላል። በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ውስጥ ‹‹በኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር ተፈጸመ›› በተባለ ጥቃት ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ቁጥራቸው ከ63 በላይ የሚሆኑ ንጹሐን ተገድለዋል። እንዲሁም በትግራይና በአፋር ክልሎች ጠረፋማ አካባቢዎች ዜጎች በየጊዜው እየታፈኑ እንደሚወሰዱ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከነዚህ እና ሌሎች መሰል ክስተቶች ተምሮ በቂ ዝግጅት፣ ጥበቃና መከላከል ማድረግ አለመቻሉ አሁን በጋምቤላ ክልል በንጹሐን ዜጎች ላይ ለተፈጸመው አሠቃቂ ድርጊት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳደረገ መገመት አይከብድም።

መንግሥት ያለበትን መሠረታዊ ግዴታዎች ማለትም የዜጎችን መብቶች በአግባቡ የመጠበቅ፣ የማክበርና የማሟላት ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነቶችን በእውነተኛነትና በተግባር ካላሳየ ተመሳሳይና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላለመፈጸማቸው ምንም ዋስትና አይኖርም።

የፌዴራልና የክልሉ መንግሥት የዚህን አረመኔያዊ ድርጊት ፈጻሚዎች በሕግ ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሁኔታ በአፋጣኝ እንዲያመቻች፣ ታግተው የተወሰዱ ሕፃናትና ሴቶች ወደ ሐገራቸው ተመልሰው ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚገናኙበት መንገድ እንዲፈለግ፣ ተገቢው የስነልቦና ድጋፍ እንዲደረግላቸው፣ በጥቃቱ ምክንያት የቆሰሉ፣ ቤትና ንብረታቸው የወደመባቸው፣ ከብቶቻቸው የተዘረፉባቸውና ከቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች ሁሉ ሰብዓዊ እርዳታ እንዲያገኙና መልሰው የሚቋቋሙበት ድጋፍ በዋነኛነት በመንግሥትና በተጨማሪም በእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች እንዲደረግላቸው ሰመጉ ጥሪውን ያስተላልፋል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)<br>
ሚያዝያ 18 / 2008 ዓ.ም.<br>
አዲስ አበባ<br>
ኢትዮጵያ

**ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!**

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ Human Rights Council